# ተወዳጅ ቴዲ! ይፈታ ቴዲ!

**ቴዲን እንወደዋለን ! ቴዲ ይፈታ!**

ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን




ቴወድሮስ ካሳሁን የምንወደው በተለየ የፈጠራ ሥራ የተዋጣለት ዘፋኝና አዝናኝ ሰው በመሆኑ ብቻ አይደለም።ከሁሉ በላይ የምንወደው ታላቅ ኢትዮጵያዊ አርበኛ በመሆኑ ነው።

ቴዲ የሚወደደው በመላ ሕዋሳቱ ሀገሩን የሚያፈቅር ወጣት ብቻ ሳይሆን እርቃኑን በቆመና ስልጣን ጥርቅም አርጎ  በጨበጠ አባገነን ስርአት ውስጥ ያለፍርሃት እውነትን የሚያዜም በመሆኑ ነው።

አሁንም ቴዲን እንወደዋለን! ምክንያቱም አልሸጠንም፤ አሳልፎ አልሰጠንም፤ ከዓለም ሀብታሞች ሁሉ ሀብታም እንዲሆን እድሉን ቢሰጡትም  ከእኛ ጋር መቆየትን መረጠ።ደስታና ጭፈራ ሊያካፍለን ፤የኢትዮጵያዊነት ዜማን ሊያንቆረቁርልን፤ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የአንድነትና የእርቅ ዜማ ሊያዜም፤የነጻነትና የነጻ መሆን መዝሙር ሊያሰማ ብሎም የመዋደድና ከልብ መቀራረብን ሊሰብክ ከእኛ ጋር መቆየትን መረጠ።

ለምን በቴዲ ላይ እምነት ጣልን? ደህና! እስኪ የተጓዘባቸውን መንገዶች መቁጠር እንጀምር….ቴዲን እንወደዋለን!  ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያን አስቀድሞ ይወዳልና።

በጣፋጭ ቅላጼው እናት ሀገሩንና ፈጣሪውን ያወድሳል ያመልካል፤በሁሉም ዜማው፤ ውዳሴውና ትይንቱ ሁሉ"ሀገሬ ኢትዮጵያ "ይላል።አረንጋዴ ፤ብጫና ቀይ ሰንደቁ የዜማወቹ ሁሉ ማሳረጊያ ናቸው።

አሁንም ቴዲን እንወደዋለን!  ለምን ቢባል በአዲሱ ሚሊኒየም በአል አከባበር ላይ የችግር ነጋዴዎች ጋር  ከውጭ ሀገር በመጣ ሻምባፓኝና ኮኛክ እጅ ለእጅ ተያይዞ ከመምነሽነሽ ይልቅ እግዚአብሔርን ማመስገን መረጠ፤ ለኢትዮጵያ አንድነትና ፍቅር ጸለየ። በመዝሙሩም የእኛን የውስጥ ልባዊ ስሜታችን ተስፋና ፍላጎት አጸባረቀ።" አበባዬ ሆይ ….ወደ አዲሱ 2ኛ ሺህ ዘመን ስለአሸጋገርከን እግኢአብሔርን እናመሰግናለን፤ከአረንጓዴው፤ብጫና ቀይ ባንዲራችን ጋር ለዘላለም እንዲያቆየን እንጸልያለን አለ።

ቴዲን እንወደዋለን! ምክንያቱም ፍጹም እውነትን ይናገራል፤ ያዜማል።"እነዚያ የውሸት አብዮታዊያን ወደ ስልጣን ወንበር ተሙለጭልጨው ወጡ፤ያመጡት ለውጥ ግን የለም።አዲስ ንጉስ " ሲል ገለጻቸው፤

ቴዲን እንወደዋለን! ምክንያቱም እነዚህ በመጥፎ ሥራ የተጠመዱ ከይሲወች አይናችን ደንቁለው ወደ ጨለማ አባገነናዊ አገዛዛቸው ሊከቱን ሲጥሩ ለፍትህ፤ ለነጻነትና ለሰብአዊ መብት እንደላባዲና ብርሀን ጨለማውን በመግፈፍ ወደ ብርሀን ጎዳና የመራን በመሆኑ ፤

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚባል የለም ።ያለ ጋራ ታሪክና ባህል በመሬት ጥግ ላየ ሰፍሮ የሚገኝ የሕዝብ ጥርቅም ነው ከሚሉን የከፋፍለህ ግዛው እርኩስ ምግባር ሰባኪዎች እንዳንጠመድ አስጠንቅቆናል፤ቴዲ ግን እንዲህ ሲል ዘፈነ"ቼ መንደፈር.... የተለያዩ ማህበረሰቦች ተቻችለው የሚኖሩበት ፤ ክርስቲያንና እስላም ተግባብቶ በሰላምና በፍቅር አብሮ የሚኖርባትን ሀገር ከኢትዮጵያ በስተቀር ሌላ የለም እንዳንረሳ "አለ።

ቴዲን እንወደዋለን! ምክንያቱም ጨካኝ፤ እርህርሄ፤ቢሶችና ቅጥረኞች ተስፋ በመቁረጥ እንድንጠፋ ሌትና ቀን ከሚዶሉቱብን በፊት በስሜት እንዳንወድቅ ያነሳሳ፤ መንፈሳችን ያደሰ፤ አንገታችንን እንድናቀና ያደረገ፤ በዜማወቹ ለልባችን ፍስሀን የሰጠ ነው።

ቴዲ በትንበያው "ቆም ብለን፤አጥብቀን ተጨባብጠን! በፍቅር ይቅርታ መባባል ከቻልን የኢትዮጵያ ትንሳኤ ቅርብ ነው "ይላል።

ቴዲን እንወደዋለን! በልዩ ችሎታ የተካነና በፖለቲካ ያልተጠፈረ እውነተኛ የሙያ ሰው በመሆኑ፤ መዝባሪና ጠማማ ወንጀለኞች የዘፈኑን ፈቃድ ፈቀዱ አልፈቀዱ ግድ የማይሰጠው ነው "ለአፍሪካ አባቶች ለኃይለስላሴና ለጆሞኬንያታ የአፍሪካን አንድነት በማራመድና ለአፍሪካ ንቅናቄ ላደረጉት አስተዋጽኦ" አድንቆ ዘፍኗል።

ቴዲን በተለይ የምንወደው ወጣቶችን ሀሜትና ቅሬታ ከፍቅር ጀርባ የሚጠቅም ነገር አለመሆኑን በማስረዳት ፤የሚወዱትን ቀጥታ በፍቅር ቋንቋ እንዲያነጋግሩ አግባብ መሆኑን መከረ "አላማሽም ለሰው..." ሲል ቴዲ ሉሁሉም ነዋሪዎችና አፍቃሪዎች በቀላል ዘዴ መልክት በማስተላለፉ፤

ቴዲን እንወደዋለን! ለምን ለገጠመን ችግርች ሁሉ አንድ መፍትሄ አለው። "ጃ ያስተሰርይያል" በዜማው የነገረን ለእኛ ትልቁ ችግር ከተለያዩ ብሄረሰብ፤

መምጣታችን፤ የመልክአምድር አቀማመጥ ልዩነት፤ ቋንቋ፤ ሀይማኖትና ፖሊቲካ አመለካከት አይደለም። ትልቁ ችግራችን ከልብ የመፋቀር እጦት ነው የቴዲ ዘፈን በዚህ ረገድ የድርሻችን እንወጣ፤ ወደ አንድነት እንምጣ፤ አንዱ ላንዱ ይቅርታ ይበል፤ እንዋደድ፤ እጃችን እንጨባበጥ፤ ለኛዋ ኢትዮጵያ ተከሻን ተደጋግፈን መሰረቱን እናስተካከል፤ ግፊታችን እናጠናክር። ቀሪውን ጃህ ይጨርሰው ጃህ ያስተሰርያል" ሲል ነው በዜማው ያስተጋባው፤

ቴዲ ወደቃሊቲ ሲአል ከመውረድ ቀደም ብሎ በመዝሙሩ የጠለቀ የእምነት ስሜቱንና ሙያውን ገለፀ የማይናወጽ እምነቱንና የኢትዮጵያ መፃኤ እድል በአምላክ መዳፍ ላይ መሆኑን አረጋገጠ "ሀሌ ሀሌ ሉያ ለእኔ ሲል በመስቀል ላይ ለሞተው እንዴት ነው ውለታውን የምከፍለው?" ሲል ውለታ ከፋይ መሆኑን በማመስገን ገለፀ።

ቴዲ ዛሬም ሁል ቀንም ከጎንህ ነን "ሀሌ ሀሌ ሉያ"

በመሆኑም የምን ነግርህ ይኸውና በታሊቲ ጨለማ አስር ቤት ባለህበት የባቢሎን ስርዓት ውስጥ አንተ የኢትዮጵያ አንበሳ ብለህ የሰየምኸው ቦብ ማርሊይ የፃፈውንና ያዜመው ዜማ ይድረስህ፤

የባቢሎን ስርዓት ደም መጣጭ ያ!/ደም መጣጭ/
ቀን በቀን የልጆችን ደም ሞጥሚጭ ያ!
እኔ አልኩ የባቢሎን ስርዓት ደም ጠጭ! ወዳቂ ስርዓት!
በስቃይ ላይ ያለን ደም የሚመጥ ያ-ኤ ኤ ኤ ኢ አህ!
ቤተ ክርሲቲያን ያንፃል፤ ዮኒቨርሲቲ ይገነባል ዋ- ኦ ኦኦህ ያ አህ! ያለማቋረጥ
ሕዝብን ማታለል ያአ ኢአ!
እኔ አልኩ ሌቦችንና ገዳዮችን ማስመረቂያ
ተመልከት አሁን የችግረኖችን ደም በመምጠጥ መሳለቂያ (የችግረኛን!)
የ ኢያ ኢያ ኤ !(ስቃዮች)
ለልጆች እውነቱን ተናገር
ለልጆች እውነቱን ተናገር
ለልጆች እውነቱን አሁኑኑ ተናገር!
ቴዲ አሁኑኑ ይፈታ! ቴዲ አሁኑኑ ካባቢሎ ነፃ ይውጣ!
የእኛ ቴዲ አሁኑኑ እንዲሄድ አድርግ! ጃህ ያስተሰርያል፤
ቴዲ ብቻህን አይደለህም።

የቦብ ሜሪሊ ዘፈኞችና የሙዚቃው ግጥሞች ለማግኘት ከዚህ በታች ያለው ይጫኑ፤

**http://www.lyricsmode.com/lyrics/b/bob marley/Babylon system html.**